# የሱ የሱ ምን አለኝ ኢያሱ

ዶ/ር ካሳሁን በጋሻው

ይህ እንደ አርእስትነት ከላይ የሰፈረው አባባል የተነገረው የወቅቱ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ልጅ ኢያሱን ገልብጠው ስልጣናቸውን ከተቆናጠጡ በኋላ በስራቸው ያልተደሰቱ፤ ሊመጣ ይችላል የተባለው ለውጥ ባለመምጣቱ ቅር በተሰኙ ቡድኖች የተባለ ነው፤ዛሬ ጽሁፌ ከላይ ስለተጠቀሱት ባለስልጣናት ሳይሆን ፤ ፕሬዝደንት ሃይለማርያምን ለመተካት ስለተሾሙት ስለ ዶ/ር አቢይ አህመድ ነው፤እኚህ ሰው በብዙ መልኩ ለኢትዮጵያ ፕሬዝደንትነት ብዙዎቻችን የምንመኘውን ቅድመ ሁኔታ በአብዛኛው ያሟሉ ግለሰብ ናቸው

፩፡ ከወያኔ ጋር አለመግባባቱ በተጋጋለበት ሰአት ቋሚ የኢህድግ አባል ሆነው ሳለ ባለፉት 26 አመታት የምንናፍቀውን ኢትዮጵያዊነትን ከድርጅት አቻቸው ከአቶ ለማ መገርሳ ጋር በመሆን መስበካቸው፤ {ልብ ይበሉ የኢሃድግ አለቆች ሲሰብኩ የነበረው ኢትዮጵያ ያላት የ100 አመት ታሪክ ነው፣ ባንዲራው ጨርቅ ነው…ላሊበላ ለወላይታ ምኑ ነው …አማራና ኦርቶዶክስ አከርካሪው ተመቷል፣ ወዘተ} ታዲያ የዚህ ድርጅት ቋሚ አባል ከሆነ ሰው በቅንፍ ከተቀመጠው ፍጹም ተቃራኒውን ነበር የነገሩን

፪፡ ትውልዳቸው ከኦሮሞው ሕብረተሰብ፣ ሃይማኖታቸው ባንድ ወገን እስልምና (በአባታቸው) በሌላ ወገን ኦርቶዶክስ (በእናታቸው) በግል ፕሮቴስታንት መሆኑ {በድጋሚ ልብ ይበሉ ኢሃድግ ሲሰብክ የነበረው ኦሮሞ ሊገነጠል ነው፣ በእስልምናና በክርስትና መሃል በተደጋጋሚ እሳት ሲለኩስ የነበረ ድርጅት ነው፤ ሕገ መንግስቱም ላይ እስከመገንጠል የሚፈቅድ ነው ኤርትራን ለማስገንጠልና ሌላውን ለማስፈራራት የተተከለ አንቀጽ፣ የአገሪቱን ወደብ አያስፈልጋትም ያለ፤ ከድንበር እየቆረጠ ለጎረቤት አገር የሚያድል…} እኚህ ሰው ግን አሁንም አመለካከታቸው በቅንፍ ከተቀመጠው ውጭ ነው፤ ሕልማቸው አይደለም ወደብ ሊያሳጣን ምስራቅ አፍሪካን እስከማሰባሰብም ይሄዳል፤ ኦሮሞ አላማው ለመገንጠል ነው የሚሉትንም ያረጋጋል- ኦሮሞና ኢትዮጵያዊነት ተነጣጥለው አይታዩም የሚሉ ናቸው፤

፫፡ዶ/ር አቢይ ለአገሪቱ መሪነት በተካሄደውን ምርጫ በሚገርም ሁኔታ አሸንፈው የወጡ ናቸው፤ { ልብ ይበሉ የወያኔ ታማኝ ታዛዥ አቶ ደመቀ መኮንን እራሳቸውን ከምርጫ ማግለላቸውና ብእዴን ዶ/ር አቢይን መምረጡ የሚደንቅ ነው} እውነትም ምርጫው በሃቅ የተካሄደ ከሆነ የለውጥ ጮራ ሊኖር ይችላል

፬፡ ዶ/ር አቢይ ወያኔን ከማናችንም በላይ በቅጡ ያውቁታል፤ በመከላከያ እስከኮረኔልነት የደረሱ፤ የወያኔ የስለላውንም ክፍል በከፍተኛ ባለስልጣንነት የመሩ በመሆናቸው ሊያጋጥማቸው የሚችሉትን ነገሮች የመገምገም አቅሙም ይኖራቸዋል የሚል እምነት አለኝ፤ ቁልፍ ቦታዎችም ላይ ታማኞች ሊኖሯቸው ይችላሉ በግል እምነቴ እስከዛሬ ኢሃድግ የሚባል ድርጅት ስለመኖሩ ከሚጠራጠሩት ዋንኛው ነኝ፤ ይህን ማለቴ ባለፉት 26 አመታት ፈላጭ ቆራጩ ብቸኛው ሕዋሃት ለመሆኑ ብዙ ማሳመኛዎችን መደርደር አያስፈልገኝም፤ እንኳን የሚጽፍ የሚያነብ ምንም ፖለቲካዊ ፍላጎት የሌለው ኑሮውን ብቻ የሚኖር ሰው ይህንን ለመታዘብ በ 24 ሰአት ኢትዮጵያ ውስጥ ቆይታ በቂ መረጃዎችን ሊያሰባስብ ይችላል፤ ቤቱ፣ ንግዱ፣ ሃብቱ፣ ስልጣኑ ኧረ ምኑ ቅጡ ሁሉ በጃቸው በደጃቸው ነው፤ አሁንም ነው፤ የአማራው፣ የኦሮሞው፣ የደቡቡና የሌሎችም ድርጅቶች ኢሃድግ ውስጥ መኖር የሕዋሃትን ስራ ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት እንጂ የመወሰን አቅም እንዳልነበራቸው ሁላችንም የምናውቀው ሐቅ ነው፤ ለዚህም ነው ነጋሶ ጊዳዳም ሆኑ ሃይለማርያም ከእንግዳ ተቀባይነት ያለፈ ስልጣን ያልነበራቸው።

አሁን ወደ ዶ/ር አቢይ አሕመድ ስንመለስ፡ ስለ ኢትዮጵያዊነት የሰበኩንን፣ አብሮ ስለመኖር ጠቀሜታ የነገሩንን፣የጎሳ ክፍፍል አደገኛነት ያስተማሩትን ፣ ስለ ሙስና የባለስልጣናት መዘፈቅ የተነተኑትን ሁሉ እርሳቸው ስልጣኑን ሲረከቡ ፍላጎታቸውን እውን ለማድረግ ምን ያህል አቅም አላቸው? ኢሃድግስ ከሕዋሃት የበላይነት የመላቀቅ አቅም አለው ወይ ? በተባራሪ እንደሚሰማው ሕዋሃት የ ዶ/ር አቢይን መሪነት ቢቀበልም ቁልፍ ቦታዎችን መከላከያ፣ የስለላ መውቅሩን፣ የውጭ ግኑኝነትና ፋይናንስን ሙሉ በሙሉ በሕዋሃት ስር እንዲሆን ከማድረጉም ሌላ የዶ/ር አቢይን አቅም መከላከያን አስመልክቶ ሊገድብ እንደሚችል ግምቶች አሉ።

ታዲያ ዶ/ር አቢይ የሕዝብ ድጋፍ ይኖራቸዋል የሚል እምነት አለኝ ከላይ እንደጠቀስኩት አቋማቸው ኢትዮጵያዊ በመሆኑ፣ ድርጅታቸው አለ፤ ብእዴን አለ፤ ደቡቡም በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ አባባል መሰረት እንደሚደግፋቸው ነው ይህ ማለት ሕዋሃትን ከፈላጭ ቆራጭነት ያወርደዋል ማለት ነው ፤(ዴሞክራሲው ከሰራ) ወይስ ወያኔ እኚህን ሰው ሕጋዊ ሽፋን አድርጎ እንደበፊቱ ፈለጭ ቆራጭ ሆኖ ይቀጥላል?

ስለዚህም እኝህ አዲስ መሪ ታማኝነታቸው ለሕዝብ ከሆነ ስልጣናቸውን እንደተቆናጠጡ ብዙ ስራ ይጠበቅባቸዋል፤

ሀ. የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ፤ በቅርቡ የተፈቱት እንኳን በድጋሚ ታስረዋል፤ ሕዝባችን የሚመኘው ሰዎች በፖለቲካ አመለካከታቸው የሚታሰሩበት፣ የሚገረፉበት፣ ያለ አድራሻ የሚሰወሩበት ግዜ ማክተም አለበት ነው

ለ. በኦሮሞና በ አማራ ክልል ያሉትን ግጭቶች በአስቸኳይ መፍትሄ ማፈላለግ

ሐ. በአስቸኳይ አዋጅ ሰበብ ሕዋሃት የዘረጋውን ወታደራዊ አገዛዝ በአስቸኳይ ማንሳት

መ. በሰላማዊ መንገድ ኢሃድግ ለሽግግር መንግስት ስልጣኑን የሚያስረክብበትን ሁኔታ ማመቻቸት

ሰ. ከመከላከያ ጀምሮ አገሪቱ ውስጥ ባሉ ትላልቅ ድርጅቶች የስልጣን ክፍፍሉን (ከትግራይ የበላይነት አላቆ) ለሁሉም የአገሪቱ ነዋሪዎች እውቀትን የስራ ልምንድን መሰረት ባደረገ መልኩ ስልጣኑን ማከፋፈል፤ ከአንድ የጎሳ የበላይነት ማላቀቅ

እነዚህን ጉዳዮች የማድረግ አቅሙን ካገኙ እውነትም የለውጥ ጭላንጭል አበራ ማለት እንችላለን፤

ካሁኑ ብዙ ሓሜታዎች አሉ፤ በኔ አመለካከት ግን ግዜና እድል ልንሰጣቸው ይገባል፤ ቀላል ሃላፊነት አይደለም፤ ሕዋሃት አሁንም ጠንካራ ወታደራዊ ቡድን አለው፤ ኤኮኖሚውንም ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስችል መልኩ ተቆጣጥረውታል (ኤፈርትና መሰሎቹ)፣ የስለላ መዋቅሩ በእጃቸው ነው፤ ለጆሮ የሚሰቀጥጡ ወንጀሎችን የፈጸሙም በመሆናቸው ስልጣን መልቀቁ ብዙ የሚያስጠይቁን ነገሮችን ያመጣል የሚል እምነትም ስለአላቸው (ትክክልም ነው) ፍራቻም አለባቸው፤ እንዚህን ነግሮች ሁሉ ግምት ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል ፤

ወደ ተነሳሁበት አርእስት ስመለስ ያኔ የሱ የሱ ምን አለኝ ኢያሱ እንደተባለው፤ እኛም እኛም ምን አለን ሓይለማርያም እንዳንል፤ ሕልሞን ለመተግበር የሚያስችል ስልጣን ካልሆነ በዚህ ሁኔታ መስራት አልችልም ብለው ስልጣኑን አስረክበዋቸው ካመንዎ ከተከተልዎ ሕዝብ ጋር ትግልዎን ሊቀጥሉ ይገባል።

የኢትዮጵያ ጠላቶች እንጂ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውነት አይጠፉም

ሰላሙን ያምጣልን

ዶ/ር ካሳሁን ቢጋሻው

Kasbeg@gmail.co